**አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ**
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት
ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት

**ABBA PAULOS I**
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot,
President of WCC and Honorary President of
World Religions for Peace


ቁጥር 6/ጵ/252/2959/2003
Ref. No.

ቀን 07-06-2003 ዓ.ም
Date

ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡-<u>በማኅበረ ቅዱሳን እየተካሔደ ካለው የሥራ ግድፈት አንፃር ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የቀረበውን ማሳሰቢያ በሚመለከት ይሆናል፤</u>

በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር እንደሚንቀሳቀስ ሆኖ የተዋቀረው ማኅበረ ቅዱሳን ከተሰየመበት የምግባረ ሠናይ ተልእኮ አላማ ውጭ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ፣

- የቤተ ክርስቲያኒቱን ማዕከላዊ አስተዳደር የሥልጣን ተዋረድ መዋቅር እየጣሰ መምጣቱን፤
- የቅርብ ተጠሪ ሆኖ ለሚሠራው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያም ሊታዘዝለት አለመቻሉን፤
- ይልቁንም የድርጅቱ ዘላቂ የሕይወት አቀጣጫ ወዴት እያመራ እንደሚሔድ ለማወቅ፤ ለመረዳትና ለመቆጣጠር አዳጋች መሆኑን በመግለፅ ከመጋረጃ በስተጀርባ ያለው ሁኔታ በቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አአስተዳደር ተመርምሮ ታይቶና ተገምግሞ ማኅበረ ቅዱሳን የሚከተለው ራእይ ርቆ ከመሔዱ አስቀድሞ የእርምት እርምጃ ይወሰድ ዘንድ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በየጊዜው የጻፋቸው ደብዳቤዎች የግል ማኅደሩን አጣበውት ይታያሉ።

ማኅበረ ቅዱሳን በሚፈጽመው የየዕለቱ የተግባር እንቅስቃሴ፤ እየኖረ የሚታይ አመራሩን የመግታት ኃላፊነት ያለባችሁ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር አካላት የሚጠበቅባችሁን ድርሻ ልትወጡ ባለመቻላችሁ የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት የጉዞ መሥመሩን በማሻቀብ ከሥልጣን ክሂሎቱ በላይ አሳልፎ በመገኘቱ፤ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሁለንተናዊ አቅም ወደራሱ አመራር አዞሮ በመታየቱ በአጠቃላይም የቤተ ክርስቲያኒቱን ህልውና በመፈታተን ላይ የሚገኝ በመሆኑ በዚህና በመሳሰለው ምክንያት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ አሁንም የተሰማውን ቅሬታ ገልፆ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም በቁጥር 101/3/2003 ከጻፈው ደብዳቤ ጋር 36 ገጽ አባሪ ማስረጃ አያይዞ አቅርቧል።

በበኩላችንም የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ከቅርብ ተጠሪው ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አስተዳደር አመራርን እያገኘ ከሚሠራ በቀር በሚይመለከተው ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት እንዲገታ፤

ABBA PAULOS (Dr.)
Patriarch of Ethiopia


251-111-111989, 251-111-550577,
Fax:- 251-111-552211
E-mail: abapaulospatriarch@ethionet.et

አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት
ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት

**ABBA PAULOS I**
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot,
President of WCC and Honorary President of
World Religions for Peace

ቁጥር ልዩ/ጽ/2592/2955/2003
Ref. No.

ቀን 07-06-2003 ዓ.ም
Date

1. በ27/1/2002 ዓ.ም በቁጥር ል/ጽ/55/2002፤
2. በ16/11/2002 ዓ.ም በቁጥር ል/ጽ/594/2002 ጽፈንላችሁ የነበረውን እናስታውሳለን፤ ይልቁንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው

- የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፤
- ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፤
- የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያው ኃላፊዎችና የድርጅት ተጠሪዎች፤
- የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊዎች፤
- የማኅበረ ቅዱሳን የሥራ ኃላፊዎችና አባላቱ በተገኙበት የማኅበሩ ጽ/ቤት የሥራ አፈጻጸም ግድፈት መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም በአጀንዳ ቀርቦ ጥልቅ ውይይት ከተደረገበት በኋላ፣ ጉባኤው ባሳለፈው ባለ11 ገጽ ውሳኔ መሠረት፤ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የማኅበሩ ጽ/ቤት ድርሻውን አውቆ ይሠራ ዘንድ እንዲስተካከል እንድታደርጉ የሚያስችል መመሪያ ቢደርሳችሁም፤ ይህን ባለማድረጋችሁ ዛሬ የማኅበሩ ጽ/ቤት የቤተ ክርስቲያኒቱን የሥልጣን ተዋረድ መዋቅር እየሸረሸረና እየጣሰ መሥራቱን በስፋት ተያይዞታል።

ለማስረጃም ያህል የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ‹‹ሁለት ልብሶች ያሉት-----›› በሚል ርእስ በቅርቡ ያዘጋጀው ፓንፍሌት በሐምሳ የአብነት ትምህርት ቤቶችና በሃያ አምስት ገዳማት ላይ የልብስ እጦት ችግር ደርሶአልና የርዳታ እጃችሁን እንድትዘረጉ ትጠየቃላችሁ ሲል ያስረዳል፤ ርዳታ ፈላጊዎቹ የአሠራሩን ሒደት ባለመረዳት አመልካቾች ሆነው ቢገኙም እንኳ የማኅበሩ ጽ/ቤት ጥያቄያቸውን ለቅርብ ተጠሪው የበላይ አካል በሪፖርት ማሳወቅ ነበረበት እንጂ በባለቤትነት ስሜት መንቀሳቀስ አልነበረበትም፤ ከዚህ አንፃር የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት እያከናወነ ያለው የየዕለቱ የሥራ ሒደት ጠቅለል ባለመልኩ ሲገመገም የቤተ ክርስቲያኒቱን ማዕከላዊ አስተዳደር ተክቶ ለመሥራት ያለውን ፍላጎት አጉልቶ ያሳያል።

ስለዚህ የምናስተዳድራቸው ማኅበራት ሁሉ ከመሥመር እየወጡ አቅጣጫቸውን ለውጠው ሲገኙ ሥርዓትን የማስያዙ ኃላፊነት የጋራችን መሆኑን በመገንዘብ የማኅበረ ቅዱሳን ጽሕፈት ቤትም ድርጅታዊ መዋቅሩን አለቦታው መጠቀሙን አቁም፤

አባ ጳውሎስ (ዶ/ር)
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት 2
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት
ABBA PAULOS (Dr.)
Patriarch of Ethiopia.
Archbishop of Axum
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot.
President of WCC and
Honorary President of World Religions Conference for Peace

☎ 251-111-111989, 251-111-550577, 251-111-565747, 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
✉ 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: aba.paulos.patriarch@ethionet.et
abagerim @yaho.com

አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት
ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት

**ABBA PAULOS I**
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot,
President of WCC and Honorary President of
World Religions for Peace


ቁጥር ል/ጽ/252/2955/2003
Ref. No.

ቀን 07-06-2003 ዓ.ም
Date

1. ቀደም ሲል ተጠይቆ የነበረውን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ገንዘብና ንብረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በዝርዝርና በጥራት አስመዝግቦ እንዲያጠናቅቅ፤
2. ድርጅቱ ዕውቅና አግኝቶ በገቢና በወጭ ካርኒ ገንዘብ መሰብሰብ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የተሠራበትን የሒሳብ ሠነድ በማቅረብ እንዲያስመረምር፤
3. በማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት እየተዘጋጀና እየታተመ የሚወጣው ጋዜጣና መጽሔት አንዳንድ ጊዜ ባልታሰበ መንገድ እየሔደ ያልተጠበቀ ችግር እያተመ ስለሚያሰራጭ ከየካቲት ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አስተዳደር ጉባኤ ሊቃውንት ሳይመረመርና ሳንሱር ሳይደረግ መጽሔቱም ሆነ ጋዜጣው እንዳይታተም፤
4. የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተላለፈው ውሳኔ በተራ ቁጥር 2 ላይ በተገለፀው መሠረት በማዕከላዊው አስተዳደር በታተመና አንድ ወጥ በሆነ የገቢና የወጭ ካርኒ ይሠራ ዘንድ ጥብቅ ትእዛዝ እንዲደርሰው፤
5. መርማሪዎቹ በሚሰማሩበት ወቅት የምርመራውን ሥራ ከመጀመራቸው አስቀድሞ ካርኒው በታተመበት ማተሚያ ቤት በመገኘት የመጀመሪያው ጥራዝ ከታተመበት ጊዜ ጀምሮ ለምርመራ ሥራ እስከተደረሰበት ድረስ ያለውን በመመዝገብና በመረዳት ወደ ሥራው እንዲገቡ፤

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ከ1-5 ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ከማስተከከያ እርማት ጥቂቱ ክፍል ስለሆነ፣ ይህን እንደመነሻ በመጠቀም እስካሁን የተላለፉትን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በመመርመር፤ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማችሁንም በማጠናከር ሥራውን ተከታትላችሁ እስከ የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም በማጠናቀቅ የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲደርሰን ታደርጉ ዘንድ በድጋሚ እያስታወቅን፤ ቀደም ሲል በ16/11/2002 ዓ.ም በቁጥር ል/ጽ/594/2002 ከተጻፈው ደብዳቤ ጋር እንዲደርሳችሁ ከተደረገው 50 ገጽ አባሪ ሌላ አሁንም 42 ገጽ አባሪና ማስረጃ ፎቶ ኮፒ የላክንላችሁ መሆኑን እንገልጻለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

ABBA PAULOS (Dr.)
Patriarch of Ethiopia,
Archbishop of Axum
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot.
President of WCC and
Honorary President of World Religions Conference for Peace

<u>ግልባጭ</u>
- ለቅዱስ ሲኖዶ ጽ/ቤት
- ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
- ለሊቃውንት ጉባኤ
- ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
  ጉዳዩን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም

<u>አዲስ አበባ</u>


251-111-111989, 251-111-550577,
251-111-565747, 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
✉ 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: aba.paulos.patriarch@ethionet.et
abagerima@yaho.com